# ምዕራፍ 9

በዳንኤል መፅሐፍ ፀሎት በጣም ትልቅ ሥፍራ ነው የተሰጠው፥ ዳንኤል በሚከተሉት ምዕራፎች ውስጥ ለፀሎት የሰጠውን ቦታ እንመልከት ።

- ምዕራፍ 2 "የሕብረት ፀሎት"
- ምዕራፍ 6 "የግል ፀሎት"
- ምዕራፍ 9 "የምልጃ ፀሎት"
- ምራፍ 12 " የማያቋርጥ ፀሎት"

ትንቢታዊ ይዞት ያለው ኑሮ ለመኖር ያለ ፀሎት ህይወት አይሆንም። ህይወታችንም ሆነ አገልግሎታችን ከፀሎት ህይታችን አይበልጥም። የግልም ሆነ የህብረት ፀሎት እግዚአብሔር ለሰጠንራዕይ ትልቅ ድርሻ አለው። የምንፀልየው ያህል ነው ኑሮአችን። ህይወታችን በፀሎት መንፈስ እየተዋጠበሄደ ቁጥር፣ ኑሮአችንም ሆነ ራዕያችን ያንኑ ያህል እየጠለቀ ይሄዳል።

ዳንኤል በቁጥር 2 ላይ፥ ***"---የኢየሩሳሌም መፍረስ የሚፈፀምበትን ሰባውን ዓመት እግዚአብሔር በቃሉ ለነቢዩ ኤርምያስ የተናገረውን የዓመቱን ቁጥር በመፅሐፍ አስተዋልሁ"*** ይላል።የዳንኤል መለኪያ በአካባቢው የነበረው ሁኔታ፣ ወይንም የውስጡ ስሜት፣ ወይንም የሰዎች አስተያየት ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ነው። ኤርምያስ የተናገረውን የተስፋውን ቃል ነው በመፅሐፍ ያስተዋለው። (ኤር. 25፡11፣ 2ዜና 36፡21፣ ኤር. 29፡10--) ዳንኤል ይህን የተስፋ ቃል በመፅሐፍ ማስተዋሉ ወደጠለቀ የምልጃ ፀሎት ወስዶታል።

## የዳንኤል ፀሎት (ቁ. 3-19)

1. ስለእግዚአብሔር ባህርይ ጤናማ የሆነ አመለካከት ነበረው። በቁጥር 4 ***"-- ቃል ኪዳንና ምህረትን የምትጠብቅ ታላቅና የምታስፈራ አምላክ ሆይ---"***፣ በቁጥር 7 ***"--ጌታ ሆይ ፅድቅ ለአንተ ነው።"***፣ በቁጥር 10 ***"--ለጌታ ለአምላካችን ምህረትና ይቅርታ ነው።"***፣

**በቁጥር 14 ***"-- አምላካችን እግዚአብሔር በሚሠራው ሥራ ሁሉ ፃድቅ ነውና፣"*** በቁጥር 18 ***"አምላኬ ሆይ በፊትህ የምንለምን ስልዙ ምህረትህ ነው እንጂ ስለ ፅድቃችን አይደለምና---"*** በቁጥር 19 ***"አቤቱ ስማ፣ አቤቱ ይቅር በል፣ አቤቱ አድምጥና አድርግ--"***

በነዚህ ቁጥሮች ላይ እንደምንመለከተው ዳንኤል የእግዚአብሔርን ባህርይ በትክክል የተረዳ ሰው ነው። እግዚአብሔር ህዝቡን በመውደዱ ፃድቅ የሆነውን ያህል፣ ሲቀጣም ፃድቅ ነው። እግዚአብሔር በሚያደርገው ሁሉ አይሳሳትም። በፅድቅ ይፈርዳል፣ ፍርዱም የማይመረመር ነው። ጳውሎስበሮሜ 11፡33 ላይ "የእግዚአብሔር ባለጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፣ ፍርዱም እንዴት የማይመረመር ነው፣ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም።"ይላል።

የእኛ ችግር ግን ብዙ ጊዜ ይኸው ነው።የእግዚአብሔርን ፃድቅነት በችግሮቻችን መሀል ማየት ይሳነናል። እንዲያውም እግዚአብሔርን ከችግራችን ጋር አዳምረን እናየዋለን። አምላካችን እግዚአብሔር ግን በሚሠራው ሥራ ሁሉ ፃድቅ ነው። የእግዚአብሔርን ባህርይ እንደዚህ ነው መረዳት ያለብን። ባህርዩን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ፣ በአግባብም ልናስተውለው ይገባል።በእግዚአብሔር ፊት የሚያጉረመርም፣ ጠማማና ክፉ የሆነ ልብ እንዳይኖረን መጠን

ቀቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እግዚአብ ሔር እርሱ እግዚአብሔር ነውና በሚያደርገው ነገር ሁ ሉ ፃድቅ ነው፡፡

2. ዳንኤል በአንድ በኩል የእግዚአብሔርን ባህርይ በትክክል ሲረዳ፣ በሌላ በኩል ደ ግሞ ስለህዝቡም ኃጢአት በትክክል አስተውሏል፡፡ በቁጥር 5 *" ... ኃጢአትን ሠርተናል፣ በድለንማል፣ ክፋትንም አድርገናል፣ አምፀንማል፣ ከትዕዛዝህና ከፍርድህ ፈቀቅ ብለናል ... "*፣ በቁ. 6 *" ... ባርያዎችህን ነቢያትን አልሰማንም፡፡"*፣ በቁ. 13 "--እውነትህን እናስብ ዘ ንድ ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔርፊት አልለመንንም፡፡" ይላል፡፡

የእግዚአብሔርን ባህርይ በትክክል ስንረዳ፣ የፅድቁንና የቅድስናውን ከፍተኛነት ስና ስተውልነው የራሳችን ኃጢአትና ጉድለት የምናየው፡፡ በርግጥ ሰው የራሱን ኃጢአትና ጉድ ለት እግዚአብሔር እንደሚያይ ማየት ሲጀምር የኃጢአትን ከባድነት ይረዳል፡፡ መንፈስ ቅዱ ስ ጉድለታችንን ወደፊታችን በሚያመጣበት ጊዜ ለማየት በጣም ቢያስፀይፍና ለጊዜው ቢያ መንም፣ ኃጢአታችንን በግልፅነት በፊቱ ማፍሰስ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እግዚአብሔር ቢሰብ ር፣ ይጠግናል፣ ዳዊት በመዝሙር 139፡23-24 ላይ " አቤቱ መርምረኝ ልቤንም እወቅ፣ፍተነ ኝ መንገዴንም እወቅ፣ በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ፣ የዘላለምንም መንገድ ምራኝ፡፡" እንዳለው ይህ የኛም ፀሎት ሊሆን ይገባዋል፡፡

3. እርሱ ያለነውርና ነቀፋ ሆኖ እያለ፣ ራሱን ከህዝቡ ጋር ሲደምር እናየዋለን፡፡ ጣ ቶቹን በሕዝቡ ኃጢአት ላይ አልቀሰረም ይልቁንም እርሱ ኃጢአት እንደሰራ አድርጎ ራሱ ን ከህዝቡ ጋር ለንሰሀ ያቀርባል፡፡ ግብዝ ሰው አልነበረም፡፡ እስቲ ይህን ፀሎት የሚፀልየው ፈሪሳዊ ቢሆን ምን ብሎ ሊፀልይ ይችል እንደነበር ለመገመት ሞክሩ፡፡ በአጭሩ በሉቃስ 18፡ 9-14 ያለውን ታሪክ መመልከቱ በቂ ነው፡፡ ዳንኤል ግን እንዲህ አልነበረም፡፡

4. የነበረው ታላቅ ሥልጣንም ይሁን፣ የተደላደለው ኑሮው ማቅ ለብሶ፣ በአመድም ላይ ሆኖ ለመፆምና ለመፀለይ አላገደውም፡፡ ወይም ደግሞ የቃሉን መገለጥም እንዳያገኝ አ ላደረገውም፡፡ በ1ጴጥሮስ 4፡7ላይ "ትፀልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ"የሚል ቃል እናገኛለን፡፡ ም ክንያቱም በብዙ ረብ በሌላቸው ነገሮች የተያዘ አዕምሮ ያለው ሰው የጠለቀ የፀሎት ህይወ ት ሊኖረው አይችልም፡፡ መዝገቡ ባለበት ልቡ ደግሞ በዚያ ይሆናል፡፡ እየፀለየም እያለ አዕም ሮው የሚዋትተው ግን መዝገቡ ባለበትይሆናል፡፡ ትርጉም ያለው ፀሎትም መፀለይ አይችል ም፡፡ ከራሱም አልፎ ሌሎችን በፀሎቱ ሊያስብ አይችልም፡፡ ስለሌሎች ሰዎች ቢፀልይም ያሉ በት ችግርና ሁኔታ በእርግጥ ገብቶት ሳይሆን ለማድረግ ያህል ነው የሚያደርገው፡፡

# በፀሎት ጊዜ

5. ዳንኤል እየፀለየ እያለ ፀሎቱ መላዕክትንም እንኳ አንቀሳቅሷል፡፡ በቁጥር 20 ላ ይ *"እኔም ገና ስናገር ስፀልይ---ገብርኤል እየበረረ መጣ፣ በማታም በሥዋዕት ጊዜ ዳሰሰኝ፡፡"* ስለሚል ገብርኤል የዳንኤልን ፀሎት በመሀል ያቋረጠ ይመስላል፡፡ እንዲያውም በቁጥር 23 ላይ፦ *"አንተ እጅግ የተወደድህ ነህና በልመናህ መጀመሪያ ላይ ትዕዛዝ ወጥቷል፣ እኔም እነግርህ ዘንድ መጥቻለሁ፣"* ይላል፡፡

የመልአኩ ገብርኤል አመጣጥ በቁጥር 23 ላይ፦*"ዳንኤል ሆይ፣ ጥበብንና ማስተዋልን እሰጥህዘንድ አሁን መጥቻለሁ፡፡"* እንዳለው ነው፡፡ ይህም የሚያሳየን ምንም እንኳን እግዚአ ብሔር ለተለያዩምክንያቶች ራዕዩን ይግለጥልን እንጂ ጥበብና ማስተዋል ደግሞ ያስፈልገና ል፡፡ ምክንያቱም ራዕዩን ማሰብ፣ ማጤን፣ ማሰላሰል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔርን አ ሠራር አስተውለን በየትኛው ዘመንና እንዴት ባለ መንገድ እንደሚፈፀም ጥበብ በጣም ያስፈ ልጋል፡፡ ሰለሞን ወደ ንጉሥነት በመጣበት ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያስተዳድርበትን ጥበብና ማስተዋልን እንዲሰጠው የፀለየው ከዚህየተነሣ ነው፡፡ ያዕቆብ በመልዕክቱ ውስጥ በም ዕ. 1፡5 ላይ *"ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚ አብሔርን ይለምን፣ ለእርሱም ይሰጠዋል፡፡"* ይላል፡፡ ጥበብና

ማስተዋል ከሌለንግን ዘመኑን መዋጀት አንችልም፤ ሲፈፅምም እንኳን ሳናስተውለው ሊያል ፍ ይችላል። የጥበብ ጉድለት የሚያሳፍር አይመስለኝም፤ ይልቁንም ሳይነቅፍ በልግስና ለሁለ - የሚሰጠው እግዚአብሔር እያለ ከነጉድለት እንዲሁ መኖር ነው የሚያሳፍረው።

እኛስ የምንፀልየው ፀሎት የእግዚአብሔርን ልብ ነክቶ የመላዕክትን ልብ ነክቶ (አን ቀሳቅሶ) ይሆን?! የእግዚአብሔርን ባህርይ በመረዳት በመንፈስ ቅዱስ የሚፀልይ ፀሎትም ሆነ ምልጃ፤ ማስጋናም የሰማያትን ልብ ሁሉ ያንቀሳቅሳል።

**ቁጥር** 24-27

***" አሁንም ነገሩን መርምር፤ ራዕዩንም አስተውል። "***

ይህ ቃል ዳንኤል በጊዜ ተረድቶት ከነበረው መረዳት ያለፈና የጠለቀ ትርጉም ያለው ራዕይ እንደሆነ ያመለክተናል። በቁጥር 24 ላይ÷ "በቅድስና ከተማህ ላይ ሰባ ሱባዔ ተቀጥ ሮአል። ስለዚህእወቅ አስተውልም።" ይለዋል። ዳንኤል ሰባ ሱባዔ ማለትም ሰባ ሳምንት በጊ ዜ የመሰለው ሰባው ዓመት የባቢሎን ምርኮ ዘመን መስሎት እንዳበቃም ቆጥሮት ነበር። ሆኖ ም ምስጢሩ ግን ከዚያም የጠለቀ ነው። የሚጀምረው በነኅምያ 2:1 ጀምሮ ባለው ክፍል ው ስጥ እንደተገለጠው ከኢየሩሳሌም መጠገንና መሠራት ነው።(445 ዓ.ዓ.) የሰባው ሱባኤ (ሳም ንት) እያንዳንዱ ቀን እንደ አንድ ዓመት ነው የሚወሰደው። ስለዚህ 69 ሳምንት በሰባት ብ ናባዛው 483 ዓመታት ይሆናል ማለት ነው። እነኚህ ዓመታት መሲህ እስከሚገለፅበት ዓመት ድረስ ያሉ ዓመታት ናቸው።(ቁ.25) ***"ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሲህ ይገደላል፤"*** ስለሚል በ69 ሳምንት መጨረሻ፤ ማለትም በ483ኛው ዓመት መጨረሻመሲህ ይገደላልየቀረ ው አንድ ሳምንት (70ኛዋ ሳምንት) ። በ69ኛው ሳምንትና በሰባኛው ሳምንት መካከል የዘመ ናት ርቀት እንዳለ ልናስተውል እፈልጋለሁ። የቀረው አንድ ሳምንት፤ ማለትም ሰባት ቀናት ማለትም ሰባት ዓመታት ሰባቱ ሊመጡ ያላቸው የመከራ ዘመናት ናቸው።

<u>በ69ኛውና በሰባኛው ሳምንት መካከል ያለው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ነው።</u> በሌላ በኩል ደግሞ ጌታ ኢየሱስ እንዳለውም "የአህዛብ ዘመን" ነው።

**ለመሆኑ የሰባው የሲባኤ ዓላማ ምንድነው? በዚህ ክፍል ውስጥ ስድስት ዓላማዎች ተገልፀዋል። (ቁ.24)

1. ዓመፃን ይጨርስ ዘንድ
2. ኃጢያትን ይፈፅም ዘንድ
3. በደልንም ያስተሰርይ ዘንድ
4. የዘላለምን ፅድቅ ያመጣ ዘንድ
5. ራዕይንና ትንቢትን ያትም ዘንድ
6. ቅድስተ ቅዱሳኑም ይቀባ ዘንድ፤ ነው።

**በቁጥር 24 ላይ÷ ***"ስለዚህ እወቅ አስተውልም፤ ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትዕዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው መሲህ ድረስ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል--- መሲህም ይገደላል---"*** ስለሚል ሰባው ሱባዔ የሚጀምረው ኢየሩሳሌምን ለመጠገንና ለመሥራት ትዕዛዝ ከሚወጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ኢየሩሳሌምን በሚመለከት አራት ትዕዛዞች በተለያየ ዘመን ወጥተው ነበር።

1. ንጉሥ ቂሮስ ያወጣው ትዕዛዝ÷ 539/536 ዓ.ዓ.

በ2ዜና፡36 እና በዕዝራ ምዕ. 1፡6

*እነኚህ ክፍሎች የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ መሠራት እንጂ የኢየሩሳሌም ከተማ መጠገንና መሠራትን አያመለክቱም። ስለዚህ ይህ ዓመት ሊሆን አይችልም።*

2. *ንጉሥ ዳርዮስ ያወጣው ትዕዛዝ፥* 519/518 *ዓ.ዓ.*

*በዕዝራ ምዕ.* 6 *ተገልጿል።*

*ይህም ትዕዛዝ ዳርዮስ ያዘዘው ካሁን በፊትም ንጉሥ ቂሮስ ምን ትዕዛዝ እንዳስተላለፈ ለማወቅ የተደረገ ጥናት ነው እንጂ በፊት ያልነውን ነገር አያመለክትም።*

3. *ንጉሥ አርጤክስስ ያወጣው ትዕዛዝ፥* 458/7 *ዓ.ዓ.*

*በዕዝራ ምዕ.* 7 *ላይ እናገኘዋለን።*

*እንዲያው ይህ ትዕዛዝ ስለከተማይቱ እንደገና መሠራት ምንም የሚናገረው ነገር የለም።*

**4. *ንጉሥ አርጤክስስ ያወጣው ትዕዛዝ፥* 445/7 *ዓ.ዓ.* በነኅምያ ምዕራፍ 2 ላይ ተ *ገልፆ* እናገኘዋለን። በዚህ ጊዜ ነው የከተማይቱ *መሠረራት የተፈፀመው።* በዳንኤል 9፡25 *መጨረሻ ላይ፥ **"እርሱዋም በጭንቀት ዘመን ከጎዳናና ከቅጥር ጋር ትሠራለች።"*** እንዳለው በ ብዙ ተቃውሞመሃል *ነኅምያና ሌሎች መሪዎች* ህዝቡም ከተማይቱንና ቅጥሯን ሠርተው የ ጨረሱት በዚህ ጊዜ ነው። ስለዚህ ሰባ ሱባዔው የሚጀምረው በዚህ ጊዜ ነው።

በቁጥር 26 *መሲሁ* ከተገደለ በኋላ፥ *"---**ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ---**"* እንዳለውና ጌታ ኢየሱስም በአገልግሎቱ ዘመንመሀል ኢየሩሳሌም በሮማውያን እጅ በ70 ዓ. ም. ፈረሰች። በዚያው ቁጥር ላይ፥ ***"እስከመጨረሻም ድረስ ጦርነት ይሆናል፤ ጥፋትም ተ ቀጥሮአል።"*** ስለሚል እስከአሁን ድረስ ጦርነት ከዚያ አካባቢ አልጠፋም። የመካከለኛ ምስ ራቅ ችግር እስከአሁን መፍትሄ ያልተገኘለት ችግር ነው።

በቁጥር 27 ላይ ግን "እርሱም (ማለትም ትንሿ ቀንድ አውሬ የክርስቶስ ተቃዋሚው) ከብዙ ሰዎች ጋር ፅኑ ቃል ኪዳን ለአንድ ሱባዔ ያደርጋል" አንዳለው የሰላም ሰው መስሎ ስለሚመጣና ምናልባትም የመካከለኛ ምስራቅን ችግር ለመፍታት ስለሚሞክር እስራኤላው ያን በዚህ ይታለላሉ። ከእርሱም ጋር ቃል ኪዳን ይገባሉ። ከሰባት ዓመቱ የመከራ ዘመን 3 1/2 ዓመት በሰላም ከቆዩ በኋላ፥*"**በሱባዔውም እኩሌታ መሥዋዕቱንና ቁርባኑን ያስቀራል**---"* እንደለው በሰባት ዓመቱ አጋማሽ ላይ ቃልኪዳኑን ያፈርሳል። ስለዚህ በአይሁድ ላይም ይ ነሣል። መሥዋዕት ለእግዚአብሔር እንዳያቀርቡ ቁርባንም እንዳይደረግ ይከለክላል። ቤተመ ቅደሱንም ያረክሳል። ብዙዎችንም አይሁድ በእምነታቸው ምክንያትይገድላል። **በመጀመሪ ያው አጋማሽ በፊት ቤተክርስቲያን ስለተነጠቀች በራዕይ 11፡1-14 ላይ እንደተገለፀው እግዘ አብሔር ሁለት የተቀቡ ነቢያትን አስነስቶ ወንጌልን እንዲሰብኩ ያደርጋል። ብዙ አስገራሚ ድንቃድንቆችንም ይፈፅማሉ። እነዚሁ ሁለት ምስክሮች በዘካርያስ 4፡11-14 ***"ሁለቱ ወይ ራዎችና ሁለቱ መቅረዞች"*** ተብለው የተጠቀሱት ናቸው። ለመጀመሪያዎቹ 3 1/2 ዓመታት በፍፁም ነፃነት ይሰብካሉ።ትንቢትም ይናገራሉ ። 3 1/2 ዓመት ካለቀ በኋላ ግን አውሬው፤ ማለትም የክርስቶስ ተቃዋሚው ሁለቱን ነቢያት ይገድላቸዋል። ዓለምም በሞላው ሁለቱ በ መገደላቸው ደስ ይለዋል። ከደስታቸውም የተነሳ ስጦታን ይሰጣጣሉ። በድናቸውም ወደመ ቃብር ሊገባ አይፈቅዱም። ዓለምም ሁሉ ያያል። ምናልባት በሳተላይት አማካኝነት በቴሌቪ ዥን ያሳዩት ይሆናል።

ከ3 1/2 ቀናት በኋላ ግን እግዚአብሔር የህይወትን መንፈስ ይሰጣቸዋል። ታላቅም ፍርሃት በምድር ሁሉ ይወድቃል። ጠላቶቻቸውም ሁሉ እያዩ ወደ ሰማይ በደመና ይወጣሉ ። በምድር ላይ ብዙ ጥፋት ይሆናል። የምድር አህዛብም "ለሰማይ አምላክ ክብርን ይሰጣሉ።"

እዚህ ላይ ልንጠይቀው የሚገባን ጥያቄ ***"ሁለቱ ነቢያት እነማን ናቸው?"*** የሚለውን ነው። አንዳንዶቹ ሞትን ሳያዩ ያለፉት ሄኖክና ኤልያስ ናቸው ብለው ያምናሉ። ሌሎች ደግ ሞ ጌታ የሱስበደብረ ዘይት ተራራ በክብሩ ተገልፆ በነበረበት ጊዜ አብረውት በግራና በቀኝ የነበሩት የህግና የነቢያት ምሳሌ የሆኑት ሙሴንና ኤልያስ ናቸው ብለው ያምናሉ ። (ሉቃስ

9፡30) ዋናው ቁም ነገሩ ግንበሰባት ዓመት የመከራ ዘመን እግዚአብሔር ቀብቶ የሚያስነሳቸው ሁለት ታላላቅ ነቢያት እንዳሉና፤በሰባት ዓመት የመከራም ዘመን ወንጌል ለአይሁድም ሆነ ለተቀሩት ህዝብ በሥልጣንና በኃይል እንደሚሰበክ ማወቁ ነው።

# 1. ንጥቀት (Rapture)

መጽሐፍ ቅድስ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለው የሚያምኑ ሁሉ ስለ ጌታ ዳግም ምፃአትም ያምናሉ። ነገር ግን በመካከላቸው የተለያዩ አመለካከት ልዩነት እንዳሉ መገንዘቡ በጣም አስፈላጊ ነው።

ጌታ የሱስ በግል እንደሚመጣ (ዮሐ.14፡3፤ 21፡22)፤ ሳይታሰብ እንደሚመጣ (ማቴ. 24፡32-51፤ 25፡1-13፤ ማር.13፡33-37)፤ በድንገት እንደሚመጣ (ማቴ.24፡26-28)፤ በአባቱ ክብር ከመላዕክቱ ጋር እንደሚመጣ (ማቴ.16፡27፤ 19፡28፤ 25፡31)፤ በድል እንደሚመጣ (ሉቃስ 19፡11-27) በግልፅ ተናግሯል።

A. ሆኖም አንዳንዶች የተሳሳተ፤ የተምታታም አምነት ስላላቸው በመጀመሪያ እነርሱን እንመለከትና ከዚያም ትክክለኛውን ነገር እንመለከታለን።

1. የጌታ ዳግም መምጣት የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ነው ብለው የሚያምኑ አሉ። በበዓለ ሐምሳ ቀን በሐዋርያት ላይ የወረደው የመንፈስ ቅዱስ መምጣት የጌታ ዳግም መምጣት ነውብለው ያምናሉ። ጌታ የሱስ (በዮሐንስ 14፡16፤ 15፡26) እንደተገለፀው “አጽናኝ የሆነው መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ” አለ እንጂ ራሱን አልላከም።

2. የአንድ ሰው ነፍስ መለወጥ የጌታ ዳግም መምጣት በሰውዬው ህይወት ውስጥ ተፈፅሚልብለው የሚያምኑ አሉ። በዮሐንስ 14፡23 ***“የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱም እንመጣለን፤ በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።”***የሚለውን እንደ መረጃ ጥቅስ አድርገው ይወስዳሉ።

ነገር ግን ይህ አመለካከት የተምታታ ነው። ብዙ ሩቅ ሳንሄድ መልዕክቶችን የፃፉት ሐዋርያት በሚጽፉበት ጊዜ የተለወጡ ሰዎች ቢሆኑም በመልዕክቶቻቸው ስለጌታ ዳግም መምጣት በግልፅ ፅፈው ነበር። ስለዚህ ንሰሃ ወደሚገባው ሰው ሕይወት መግባቱ የጌታ ዳግም ምጽዓት አይደለም።

3. የኢየሩሳሌም በ70 ዓ.ም. እንደ ጌታ ትንቢት መጠን መፍረስ የጌታ ዳግም ምጽአት ነውብለው የሚያምኑ አሉ። ማቴ. 16፡28 በዚህ መልክ ነው የሚተረጉሙት። የኢየሩሳሌም ከተማ መፍረስ በማቴ. 24፤ ማር. 13 እና ሉቃስ 21 ላይ እንደተገለጸው ከጌታ መምጣት ጋር የተያያዘ ቢሆንምየጌታ ዳግም መምጣት በግል፤ የሚታይ ሁኔታ እንደሚገለፅም የምንጠብቀው ታላቅ ተስፋ ነው። 1 ዮሐንስ መልዕክትና የዮሐንስ ራዕይ መፃህፍት ሁለቱም ከኢየሩሳሌም መፍረስ በኋላ የተፃፉ ሆነውእያለ የጌታ ዳግም ምፅአት አስረግጠው ይናገራሉ።( 1ዮሐ.2፡28፤ 3፡2፤ ራዕ.1፡7፤ 3፡11፤ 22፡12-20)

4. እያንዳንዱ ሰው ሲሞት ወደ ጌታ ስለሚሄድ የጌታ ዳግም ምፅአት ነው ብለው የሚያምኑ አሉ።ማቴ. 24፡42 እንደ መረጃ ጥቅስ አድርገው ይወስዳሉ። ይህ ግን ማለትም የሰው መሞት ከጌታ ዳግም ምፅአት ጋር ልናምታታው የሚገባን ነገር አይደለም። ሁለቱም የተለያዩ ነገሮቸ ናቸው። በመፅሐፍ ቅዱስ ሞት እንደ ጠላት ሲቆጠር (1ቆሮ 15፡25፤ ዕብ.2፡1)፤ የጌታ ዳግም ምፅአት ግን የከበረ ተስፋ ነው።(ቲቶ2፡1-13) በሞት ጊዜ መቃብር ሲዘጋ፤ በጌታ ዳግም ምፅአት ግን መቃብር ይከፈታል።( ዮሐ.5፡28፤ 1ተስ.4፡16)

5. የዓለም በሙሉ *"መንግሥትህ ትምጣ"* ብሎ ለመፀለይ መለወጥ የጌታ ዳግም ምፅ አት ነው ብለው የሚያምኑ አሉ:: ሆኖም በመጽሃፍ ዓለም ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የጌታ ዳግም ምፅአትሲቃረብ ከእግዚአብሔር እንደሚሄድ መረጃ ጥቅሶች አሉ:: (ሉቃስ 18:8፤ 2 ተስ.2:3-12፤ 1ጢሞ. 4:1፤ 2ጢሞ 4:1-4፤ 2ጴጥ.2:1) እንዲያውም የኖህ ዘመንን ይመስላል:: (ሉቃስ 17.26-30)

# 2. የጌታ ዳግም ምፅአት

በመጀመሪያ ጌታ የሱስ ሁለት አመጣጥ እንዳለው መግለፁ በጣም አስፈላጊ ነው:: በመጀመሪያ ወደ አየር ይመጣና በአየር ላይ የሚከናወኑ ነገሮች አሉ:: በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በገሃድ ወደመሬት ይመጣል:: ስለዚህ ሁለቱን ነጣጥለን በዝርዝር እንመለከታቸዋለን::

**ሀ . በአየር ላይ/ ወደ አየር መምጣቱ፥** (1ተስ 4:13-18)
ጳውሎስ በተስ.4:16 ላይ፥ ጌታ ራሱ በትዕዛዝ በመላዕክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መላዕክት ከሰማይ ይወርዳልና፤ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚህም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን:: እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን::" ይላል:: ሌላም 2ተስ.2:1፤ ዮሐ.14:3 1ቆሮ.15:51-54 መመልከት እንችላለን ::

የዚህ መምጣቱ አላማ የራሱ የሆኑትን ለመውሰድ ነው:ቤተክርስቲያን ትነጠቃለች: ገ ጌታም በአየር እንቀበለዋለን:: ሁለት የሚከናወኑ ነገሮች አሉ:: በመጀመሪያ በጌታ የሞቱት ይነሣሉ፤ ከዚያምእኛ በሕይወት የምንኖር <u>በቅፅበት አይን እንለወጣለን::</u> (1ቆሮ.15:51-57) ስለዚህ ጌታን በአየር እንቀበለዋለን:: ከዚህ በኋላ በ1ጴጥሮስ 4:17 ***"ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነስቶ የሚጀመርበት ጊዜ ደርሷልና፤"*** እንዳለው ቅዱሳን ሁሉ ለፍርድ ይቀርባሉ::ይህ ፍርድ ዓለም እንደሚፈርደው ፍርድ ሳይሆን ሽልማት (ብድራት) ለመቀበል ወይንም ላለመቀበል ነው እንጂ ለመዳን ወይንም ላለመዳን አይደለም:: ይህ እንዳለቀ በራዕይ 19 ላይ እንደተገለፀው የበጉ እራት ይከናወናል:: ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ ነች::(2ቆሮ.11:2፤ ኤፌሶን 5:24፤ 32፤ ራዕይ 19:6-9)

**ለ . ወደ ምድር በግልፅ ዳግም የሚመጣበት ጊዜ፥** በዘካርያስ 14.4 ተራራ ፥ ***" በዚያም ቀን እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረ- ዘይት ላይ ይቆማሉ"*** ይላል ::እንደገና በሐዋ. ሥራ 1:11 ላይ ሁለቱ መልዕክት ደቀ መዛሙርቱን ***"... ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው.."*** ሌሎችም መረጃ ጥቅሶች (ማቴ. 19:28፤ 24:29-31፤ 25:31-46፤ ዘካርያስ 12:10-14) በራዕይ 1:7 ላይ፥ ***"እነሆ <u>ከደመና ጋር ይመጣል</u>፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል..."*** ይላል.. ***"...ከደመና ጋር ይመጣል"*** እንዳለው ዳግም በግልፅ ሲመጣ የራሱ ከሆኑት (ከቅዱሳን) ጋርይመጣል:: ኢዩኤል 3:11 ላይ፥ ***"...ኃያላኖችህን ወደዚያ አውርድ::"*** ይላል:: በ1 ተሰ. 3:12 ላይ ደግሞ፥ ***"ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ሲመጣ ..."*** የሚል ቃል እናገኛለን:: በይሁዳ 14 ላይም፥ ***"---ኃጢያተኞችንም ሁሉ እንዲወቅስ <u>ከአዕላፍት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል</u> ብሎ ለእነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ:: "*** የሚልቃል እናገኛለን::

**ሐ** . ዳግም ለቅዱሳኑ በሚመጣበት ጊዜ እስከዚያን ድረስ አመጽ በሙላት እንዳይስለጥን ሲቋቋምና ሲቆጣጣር የነበረው መንፈስ ቅዱስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ይወሰዳል.. ለዘህ ነው በሰባት ዓመቱ የመከራ ዘመን አውሬው (የክርስቶስ ተቃዋሚው) እንደፈለገ የአመፅን ሥራ የሚያከናውነው በ2ተስ.2.6-8 የሚለውን እንመልከት፥ ***"በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ : የአመፅ ምስጢር አሁን ይሠራልና፤ ብቻ ከመንገ***

*ድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ.. በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፤ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤"*

# 3. የጌታ ዳግም ምፅአት ዋና አላማዎች ፥

ቀደም ብለን እንደተነጋገርነው ጌታ ኢየሱስ ወደ አየር የሚመጣበትና፤ ወደምድር የሚመጣበት ወቅቶች ሁለት የተለያዩ ወቅቶች እንደሆኑ ተመልክተናል.. የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያንን ለመንጠቅ ነው..ሁለተኛው ግን የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት..

1. *ራሱንና የራሱ የሆኑትን ለመግለፅ ነው፥* (1ተስ.3.12) ቢያንስ *ላለፉት ሃያ ክፍለ ዘመናት በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እንደ ታየው ልናየው ባንችልም ዳግም ሲመጣ ግን በግልፅ ይታያል የወጉትም ሁሉ ያዩታል..* (ኢዩ.3.11፤ ዘካ.14.5፤ 1ተስ.3.13፤ ይሁዳ 14፤ *ራዕይ* 1.7፤ ዘካ.12.10) እንዲያውም ማቴ. 24.30 ላይ፥ ***"የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤"*** በዘካ.14.5 ላይ ***" ... አምላኬ እግዚአብሔርም ከቅዱሳኑ ጋር ሁሉ ይመጣል ፡ "*** እንዳለው በክብርና በግርማ ከቅዱሳኑ ጋር ይገለፃል..

2. በአውሬው፤ በሐሰተኛ ነብዩና በሠራዊታቸው ላይ ለመፍረድ፤ በራዕይ 16.12-16 ላይ፥ ***" ... ከዘንዶውም አፍና ከአውሬው አፍ ከሐሰተኛም ነብይ አፍ ... ሦስት ርኩሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ፤ ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና፤ በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔርቀን ወደሚሆነው ጦር እንዲያስከትቱዋቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይመጣሉ ። ... በዕብራይስጥ" አርማጌዶን " ወደሚባል ሥፍራ አስከተቱዋቸው ፡ "*** ይላል ። የኢየሩሳሌምን ከተማና አይሁድን ይይዙ ዘንድ ይሰበሰባሉ (ዘካ.12.1-9፤ 13.8-14.2) *ነገር ግን ድልን ለማድረግ ሲቃረቡ ጌታ የሱስከሠራዊቱ ጋር ከሰማይ ይገለፃል (ራዕይ* 19. 11-16) በተለይም በቁጥር 16 ላይ "በልበሱና በጭኑም የተፃፈበት፥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶቸም ጌታ የሚል ስም አለው ፡ " እንዳለው ንግሥናው በሁሉ ዘንድ የታወቀ ይሆናል ፡ በ *አርማጌዶን ጦርነትም ጊዜ ታላቅ ድል ይቀዳጃል ፡ (መዝ*.2.3-9፤ 2ተስ.2-8፤ *ራዕይ* 19.21፤ 2ተሰ.1.7-10)

3. ሰይጣንን ለማሰር ነው፥

አውሬውና *ሃሰተኛው ነብይ ወደ እሣት ባህር ሲጣሉ፤ ሰይጣን ደግሞ ለአንድ ሺ አመት ይታሠራል ፡ (ራዕይ* 20.1-3) *ምንም እንኳን ጌታ የሱስ በመስቀል ላይ የሰይጣን ራስ ቢቀጠቅጥም፤ እስከዚህ ጊዜ ድረስ አይታሰርም..* (ዮሐ.16.11፤ ኤፌ. 2.2፤ 2ቆሮ. 4.4፤ 1ጴጥ. 5.8.) ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ ግን ለአንድ ሺ አመትግን ይታሰራል..

4. እስራኤልንም *ለመታደግ ነው የሚመጣው፥ ጳውሎስ በሮሜ* 11.1 ላይ ***"እግዚአብሔር ህዝቡን እስራኤልን አልጣለም ይላል ፡ በቁጥር 25 ላይ፥" ... ይህን ሚስጢር ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፤ የአህዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ ድንዛዜ በእስራኤል በአንዳንድ በኩል ሆነባቸው፤ እንደዚሁም እስራኤል ሁሉ ይድናል፤ "*** እስራኤልን ሁሉ ይታደጋል፤ ይሰበስባልም ..(ኢሳ.11.11-14፤ 62.4፤ ኤርምያስ 31.35-37፤ 33.14-22፤ ህዝ.37.18-25)፤ ከእነርሱም *ጋር ቃል ኪዳን ያደርጋል ፡* (ኢሳ. 66.8፤ ኤር. 31.31-34፤ ዘካ.12.10-13.1፤ ዕብ.8.8-12) ,የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ሁሉ ከሙታን የሚነሱት በዚህ ጊዜ ነው ፡ (ዳንኤል 12.2)

5. በዓለም *መንግሥታት ላይ ለመፍረድ ነው የሚገለፀው፥* ይህ ፍርድ በራዕይ 20.11-15 ላይ እንደተገለፀው የነጭ ዙፋን ፍርድ አይደለም ፡ የሺ ዘመን መንግሥት ከመጀመሩ የሚፈርዱበትፍርድ ነው ።

6. ፍጥረትንም ሁሉ ለማዳንና ለመባረክ ነው፥ ጳውሎስ በሮሜ 8.19-15 ላይ እንደ ገለፀው፥ *“የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና ፤ ....ፍጥረት ራ ሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲ ደርስ ነው.. ፍጥረት ሁሉ እስከአሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለን ፤ ... ”* ይላል ። ይህ ክፍል የሚያሳየን በአዳም ምክንያት የተሸከሙትን መርገም ከላያቸው የሚነሳበትን ዘመን በመቃተት እየተጠባበቁ እንዳሉ ነው ፡ የመሬት መንቀጥቀጥ፤ የአየር መበላሸት፤ የሰብል መጥፋት፤ የአውሬዎቸ መጨካከን፤ ይህን ነው የሚያሳየን.. በኢሳያስ 1 1.1-9 የተገለፀው ሁኔታ ጌታ የሱስ ደግሞ ሲመጣ የሚያገኙትን ፈውስ ይጠባበቃሉ.. ጌታ ሲመጣ ነው ፍጥረት ሁሉ የሚፈወሰው ።

7. የራሱንም መንግሥት ለማቆም ዳግም ይመጣል፥
በዳንኤል 2.44 “ የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል፤” ያለው ይፈፀ ማል ።